# በአንድነት ስንቆም ሃያል ነንና
# ዛሬም እንደወትሯችን እናብር!!
## መርሻ ዮሴፍ

እኛ ኢትዮጵያውያን/ት ሁላችንም በቅርብ ቀናት ዉስጥ ከሀገራቸው በመሰደድ ላይ ባሉትና በተሰደዱትም ወገኖቻችን ላይ በተለያዩ ስፍራዎች በአሸባሪዎችና በሌሎችም የጥፋት እጆች በደረሱት በካራ የመቀላት፣ በጥይት የመገደል፣ በእሳት የመቃጠል፣ ባህር ዉስጥ የመስጠም፣ ... የበርካታ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣ ልጆቻችን ሕይወት መጥፋት እጅጉን እንዳሳዘነን ዕሙን ነው። ሌሎች ወገኖቻችን ደግሞ በኅሊና ቢስ ወሮበሎች እጅ የመሰቃየት፣ የመተልተል፣ የመገደል(በአምባገነኖች ሥርና መንግሥታዊ ሥርዓታቸው በተናጋባቸው እንደ ሊቢያ፣ ደቡብ የመን፣ ... መሰል ሀገሮች ዉስጥ ጭምር) በጦርነቶችና  በከፍተኛ ጭንቀት ዉስጥ በዘወትር ሰቀቀንና ስጋት ላይ ይገኛሉ። እንደዚህ በአጭር ጊዜ ዉስጥ በበርካታ ስፍራዎች በዜጎቻችን ላይ ተደጋጋሚ የሞትና ሊላም አደጋ ስላላጋጠመን (ወይንም ደርሰው ስላላስተዋልናቸው) የሰሞኑ በሀገር ዉስጥና ከሀገር ውጭ ያለውን በኅሊናው የሚዳኝ ዜጋ ሁሉ እጅግ አሳዝኖታል፣ ውስጠ ኅሊናውን ቆጥቁጦታል፣ ያለጥርጥርም አስቆጥቶታል፣ ሩህሩሁን ወገናችንን አንዘፍዝፎታል፣ የመንዳታችን ጠቅላል ድምርና ቁልሉም አስመርሮታል።

እንደዛሬው ባይሆንም ከአንድ ዓመት በፊት በሳውዲ ዓረቢያና በሌሎችም ዓረብ ሀገሮች ዉስጥ ተቀጥረው ግልጋሎት በመስጠት ላይ በሚገኙት ወገኖቻችን ላይ በደረሱት የግፍ፣ የዕብሪትና የድፍረት ርምጃዎች ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ምሬትና ቁጣ በተቃውሞ መነሳሳትም አሳይተን ነበር። አብረን በመጮሃችን ብቻ ለጊዜውም ቢሆን የወገኖቻችን ስቃይ ጋብ እንዲል፣ እንዲቀንስ አድርገናል። ነገር ግን በወቅቱ የተጀመረውን መነሳሳት ወደ ቀጣይ የተደራጀ ሁሉንም ተቆርቋሪ ሃይሎች ወዳቀፈ የኅብረት እንቅስቃሴ ስላላሳደግነው፣ በዚያው ስፋትና ተሳታፊነት ደረጃ ስላልቀጠልንበት፣ በኢትዮጵያውያን/ት ላይ የሚደርሰውን የግፍ ዱላ ፈጽሞ እንዲቆምና ግፉም እንዲመከን አላደረግንም።

ሰሞኑን ኢትዮጵያ ዉስጥ በበርካታ የሀገራችን ክፍሎች፣ በየከተሞች ሕዝቡ ከሚገልጸው ትክክለኛ የሀዘን፣ የብስጭት፣ የቁጣ ስሜቶችና ሃሳቦች፣ ነጻ በሆኑ መገናኛ ብዙሃኖች ከሚነገሩትና ከሚጻፉት፣ ከአብዛኛዎች እንደምንሰማውና እንደምናየው፣ የደረሰው ግፍና በደል ኢትዮጵያውያንን ዳር እስከዳር አስደንግጧል፣ አሳስቧል፣ እያነጋገራቸውም ይገኛል። ስደትና ፍልሰት ስላላቆመ ከስደትና ፍልሰት ጋር ተዛማጅ የሆኑት በወገን ላይ የሚደርሱት በደሎችና ጉዳቶች አልቆሙም፣ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ላይቆሙም ይችላሉ። ልናስቆማቸው የምንችለው ግን እኛው ራሳችን ነን። ማንንም መውቀስ፣ በማንም ላይ ጣታችንን መቀሰር የለብንም፣ በመጀመሪያ ደረጃ ተወቃሾች ራሳችን፣ ሁላችንም፣ ነንና!!!

አንዳንድ ኢትዮጵያዊ ምሁራን፣ የህወሓት/ኢህ አዴግ መንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የኃይማኖት መሪዎች ጭምር ስደት ከጥንት ጀምሮ የነበረ፣ ዘላለማዊ፣ የሚቀጥልም ስለመሆኑ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ስደትን ያኔም ሆነ አሁንም ምን እንደሚያመጣው ግን ከጥቂቶች በስተቀር አፍረጥረጠው መናገር ከሚገባቸው ከሁሉ በትክክል መነገሩን አልሰማሁም። ግፍ፣ በደል፣ እመቃና ጭፍጨፋ ናቸው፣ ከድህነትና ችግር በባሰ ደረጃ ህዝብን ለፍልሰትና ለስደት የሚዳርጉት። ሰው ነፃነቱን ሲነጠቅ፣ የመኖር መብቱ ጭምር ሲያጣ፣ የዕምነት መብቱን ሲነጠቅ፣ በመረጠው አካባቢ አትኖርም ሲባል፣ ሰብዓዊ መብቶቹ ሲረገጡ፣ በሀገሩ ሡርቶ በእኩልነት የመጠቀም የዜግነት መብቱን በአድላዊና አምባገነናዊ ሥርዓት ሲነጠቅ፣ ... ሁኔታዎቹ እያስመረሩት፣ የነበረው በሀገሩ የመሻሻልና ተደስቶ የመኖር ተስፋው ይሟጠጥና ይሰደዳል።

ውድ ወገኖች፣ እባካችሁ፣ ሁላችንም ለዛሬውና ለነገው ትውልድ ስንል ለኅሊናችን እንገዛ፣ በኅሊናችንም እንመራ። ስንት ጊዜ መጮህና ማልቀስ፣ ምን ያህልስ ማንባት አለብን?! ስንት ጊዜስ ሌሎችን፣ በጥቅማቸው የታወሩ ባዕዳንን በመማጸን ላይ ተስፋ ማድረግ አለብን፣  ስንት ጊዜ ነው በኅሊና ቢስ የአምባገነን መንግሥታት ባለሥልጣኖችና አፈቀላጤዎች ያልተገራ አፍ የምንዋረደው፣ የምንዘለፈው?! ጭራሮ እንኳን በተናጠል እንጂ ችቦ ወይንም ሽጌ ከሆነ፣ በአንድ ላይ ተስብስቦ ከታሠረ፣ አይሰበርም። ይህን ዕውነታ እንዴት አንረዳም? ታዲያ እኛን ምን ነካን?! ሁላችንም እየጮህን፣ ሁላችንም የእንባ ከረጢታችን እስከሚሟጠጥ እያነባን፣ ነገር ግን አብረን መክረን ለመሠረታዊ ችግሮቻችን በጋራ መፍትሄ መሻት ለምን አቃተን። "ላለመግባባት ተስማምተዋል" የሚባለው ተረት ለኀረቤቶቻችን፣ ዐረቦች፣ የተተወ ነበር የሚመስለኝ?! ዛሬስ እኛም ከእነሱ ብሰን በመከባበር መወያየት፣ ለራሳችን፣ ለጋራ ሀገርና ለጋራ ወገን ሲባል መተባበር፣ በጽሞና መደማመጥ፣ ተሳነን። የሀገራችንን መሠረታዊ ችግሮች፣ ለድህነት፣ ለነፃነት መገፈፍ፣ ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መረገጥ፣ በመሠሪ ጎሰኞች ርስበርስ እንድንናቆር እየተደረግን ፣ ለእነሱ ዝርፊያ፣ ሙስና፣ ድብደባ ተዳርገናል። የሀገርና የወገን ፍቅር ስለሌላቸው፣ በወገን ዕልቂት የፖለቲካ ቁማር መጫወት ያምራቸዋል። የማያባራ ስደትና ፍልሰት እያመጡብንም ነው። ይብቃ እንበላቸው፣ እናስቁማቸው!!  አሁን ቃል ብቻ አይበቃም፣ በተግባር የህዝቡን የማያወላውል ጥሪ ተቀብለን በአንድነት ልንቆም፣ በአንድነት ልንሠለፍና ልንታገል ይገባል እላለሁ።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት እጅግ የባሰም አደጋ ተጋርጦብናል ብዬ እሰጋለሁ። ”የሰይጣን ጆሮ ይደፈን” ብዬ ብገልጠው ይቀለኛል። አሁን ያለውን የበሸቀጠ የህወሓት መራሽ ዘረኝነት ቶሎ ካላመከንን፣ የቂምና የበቀል ተግባሮችን ካላስቆምን፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መሀል የዘር-እልቂትን ሊያስከትልብን የሚችል የጥላቻ ውቅያኖስ እየፈጠሩልን ነው። ሙት ወቃሽ አትበሉኝና፣ ያ ኋላቀር የጎሠኛነት መርዝ ዘርቶ ያለፈው ሟች ጠቅላይ ሚንስቴር፣ ያኔ ለኢትዮጵያውያን ይመኙልን የነበረው፣ በአንዳንድ ስፍራዎችም በሎሌዎቹ አስጀምሮት ከሸፎበት የቀረው፣ የዘር ዕልቂት በድሁር ወራሾቹ፣ ዓእምሯቸው የጫጫባቸው ፍጡሮች አማካይነት፣ በዚች ታሪካዊት ሀገራችን ዉስጥ ሊከሰት ይችላል ብዬ እሰጋለሁ። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የማያወላውለውን ሠፊውን የትግራይ ሕዝብ፣ ከእነዚህ የህወሓትን አመራር በውስጣዊ ሴራና ምንጠራ ተቆጣጥረው ለሁላችንም ጥፋትን እያመጡ ካሉት ጥቂት የገዥው ቡድን አባላት ለይተን ማየት እንደሚገባን፣ በቂምና በበቀል ስሜቶችም ልንመራም በጭራሽ እንደማያስፈልግ፣ በአጽንዖት ልገልጽ እወዳለሁ።  በፍጹም በኢትዮጵያውያን መሐል፣ በሌሎች አንዳንድ ሀገሮች ውስጥ የታየው ዓይነት በዘር ተለያይቶ፣ የርስበርስ መጎዳዳትን የሚያመጣ ግጭት መኖር የለበትም ብዬም አምናለሁ። በህወሓት ዉስጥ ካላችሁት አባላት መሀል የተሳሳታችሁትን፣ እያጠፋችሁ ያላችሁትን፣ በመገንዘብ ዛሬም ከሊሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችሁ ጋር መወገን እንደሚገባችሁ ተገቢውን የእርምት ርምጃ ከሌሎቻችን ጋር ሆናችሁ እንድትወስዱ ጥሪዬን አቀርባለሁ። ታዲያ ለሁላችንም ሳይረፍድብን እንድታስቡበት እጠይቃለሁ። አበው "ሳይቃጠል በቅጠል" እንደሚሉት ችግሮቻችንን ዛሬውኑ እንጋፈጣቸው እላለሁ። የህወሓት ፍንካች የሆነው፣ ችርችም ቡድን፣ በሚወስዳቸው ፀረሕዝብ የግፍ ተግባሮች አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመሯል፣ ተቆጥቷልም። ጥቂት ሁኔታውን በበቂ ያልተረዱ፣ "ወታደራዊ ሃይል ሁሉን ነገር የሚወስን የሚመስላቸው" ተላሎች እሳቱን ሊጭሩና የርስበርስ ፍጅቱንም ሊያቀጣጥሉት ስለሚችሉ፣ በሁሉም ወገን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊኖር ይገባል እላለሁ። ሚሊዮኖችን መግደል ስለማትችሉ፣ እናንተም ጠፍታችሁ፣ ሀገራችንን ታጠፋላችሁ!!!

ሰሞኑን በሚሰደዱት ወገኖቻችን ላይ በደረሰው፣ ሁሉንም ባሳሰበ የወቅቱ የጋራ ችግር ሳቢያ ኢትዮጵያውያን፣ ተሰባስበን፣ ሁላችንም በችግሮቻችን ላይ በጋራ እንድንመክር፣ ዘላቂ መፍትሄም ለማግኘት በቁርጠኛነት እንነሳ እላለሁ። የሀገራችንና የወገናችን ጉዳዮች ሁላችንንም የኢትዮጵያ ዜጎች ይመለከተናል፣ ሊያሳስበን ይገባል፣ የዜግነት ሃላፊነታችንን ልንወጣም ይገባናል።

ኢትዮጵያዊነትን ገዥዎቻችን ሊሰባብሩትና ሊያጠፉት ቢጥሩም፣ ዛሬም ሕያውና አልበገር-ባይ እንደሆነ፣ ከአለት የጠነከረ መሆኑ ዓይነ-ልቦናው ለተከፈተ ሁሉ በገቢር እየታየ ያለ ነው። ኢትዮጵያዊነት በሀገር ፍቅር ላይ፣ የሀገር አንድነትንና ሉዓላዊንትን አላስደፍር በማለት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሕዝቡም የርስበርስ መተሳሰብና፣ መደጋገፍና መተሳሰር፣ በችግርና በመከራ ወቅትም አብሮ በመቆም እየተገለጠ ነው። ህወሓት ከሃያ ሁለት ዓመት በላያ በዘርና በሃይማኖት ከፋፍሎ ሊያጋጭና ሊያባላ ቢጥርም፣ ዛሬ ሙስሊምና ክርስትያን ኢትዮጵያውያን አንድነታቸው የማይሰበርና ጽኑ መሆኑን፣ የሞት ጽዋን አብሮ በመቀበል፣ በአጋርነት በአሸባሪዎች እጅ አብሮ እስከ መቀላት ድረስ በመሄድ አረጋግጠውታል። የዚህ ዓይነቱ ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ነው የኛም የወደፊቱ የአንድነት ትግላችንና ድላችን የማይናጋ መሠረት ሊሆን የሚገባው።

"እሱ ማነው እንደዚህ የሚወተውተው ለምትሉት፣ እኔ መርሻ ዮሴፍ እባላለሁ። የኢሕ አፓ ዴሞክራሲያ አባል ነኝ። ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ ደግሞ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ" መስራች አባል ነው። እኔ ግን በግለሰብ ደረጃ አባል ከመሆኔ በስተቀር በሁሉቱም አካሎች በአሁኑ ወቅት በአመራር ደረጃ እየተሳተፍኩ አይደለሁም። ስለዚህም በድርጅቱም ሆነ በሸንጎው ስም ሳይሆን በግለሰብ ደረጃ ነው ሃሳቤን የማቀርበው። አባል የሆንኩበትን ድርጅት፤ የኢሕ አፓ ዴሞክራሲያዊን ዓላማዎችና የሸንጎውን መሰባሰቢያ አንኳር ሀገራዊ ዓላማዎች፣ እንዲሁም አሁን ሸንጎው እያካሄዳቸው ያሉትን የማሰባሰብ ጥረቶችና ስራዎች የምደግፈው በሙሉ ልብ ነው። ታዲያ ሸንጎው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ስላላሰባሰበ በዚህ አጋጣሚ የተደራጁት ሃይሎች በሙሉ ቢሰባሰቡ፣ በተለይም ህወሓት የፈጠረውን የመከፋፈያ አጥር ሰብረን፣ በሀገር ዉስጥና ከሀገር ውጭ፣ ሕጋዊና ህገወጥ፣ ወ.ዘ.ተ. የሚሉትን አጉል መሰናክሎች ተራምደንና አፈራርሰን ጠንካራ፤ ሁሉን አቀፍ ኅብረት ለመፍጠር መቻል አለብን ብዬ አምናለሁ። በገዥው ህወሓት/ኢህ አዴግ ዉስጥ የተሰባሰቡት ቡድኖች በዘርና በሃይማኖት፣ እንዲሁም የተለያዩ ስሞችን በመለጠፍ ተቃዋሚ ኃይሎችን ከፋፍለውና ነጣጥለው፣ አምባገነናዊና በሙስናም የነቀዘ አገዛዛቸውንና ውሽልሽል ስርዓታቸውን ዕድሜ ለማስረዘም ነው የሚጥሩት። እኛ በትንንሽ ጥቃቶች ልንሸበር፣ በጊዜአዊ የብልጣብልጥ መደለያዎች ልንታለልና ልንዘናጋ፣ ፈጽሞ አይገባንም እላለሁ። ያለመደራጀት፣ ያለመሰባሰብ፣ ያለጠንካራ ኅብረት፣ ያለጽናት፣ ያለቀጣይ ትግል፣ ያለመስዋዕት፣ ... ድልን መቀዳጀት ደግሞ ዘበት ነው። ግልጽ የሆኑ ሀገራዊ ዓላማዎችን አንግበን፣ በአንድ ጠንካራ ኅብረት /ጥምረት ዉስጥ ተሰባስበን፣ ተገቢውን መስዋዕት ሁሉ ለመክፈል ተዘጋጅተን፣ እስከ ድል ድረስ በፅናት ለመታገል ቆርጠን መነሳት አለብን እላለሁ።

በግለኛነት፣ በስግብግብነትና በዘር ጥላቻ ታውረው፣ በሙስና ተጨማልቀው፣ ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉት ገዥዎች ዓይነ-ኅሊናቸው የተጋረደ ይመስለኛል። ከእነሱ በፊት በሌሎች ሀገሮችም የነበሩ አምባገነኖች ስለህዝብ ችግር፣ ስለህዝቡ ፍላጎት፣ ስለህዝብ አስተያየት፣ ስለህዝብ ጥቅም ደንታ ኖራቸው አያውቁም። የኛዎች ገዥዎች ደግሞ ወገናዊ ስሜትና ሰብዓዊ ርኅራሄም የነጠፈባቸው ናቸው!! አምባገነኖች ህዝቡ የሚለውን ሊያዳምጡ የሚገደዱት ተባብሮና ተደራጅቶ ሲነሳሳባቸው ብቻ ነውና አሁንም ለእኛ ኢትዮጵያውያን ያለው፣ የተሻለ መንገድ ሕዝቡ ተባብሮ በአንድ ላይ፣ በግብታዊነት ሳይሆን ተደራጅቶ፣ በመነሳት ነፃነቱንና ሰብኣዊ ክብሩን፣ ፣ የተነጠቀውን ሙሉ የዜግነት መብቱንና የጋራ ጥቅሙንም ሊያስከብር ሲችል ነው።

ሕዝብ  በርግጥም ሃያል ነው። አብሮ ሲቆም፣ ሲያብር፣ የማይበገር ኃይል አለው። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ በታሪኩ ደጋግሞ ያረጋገጠው ስለሆነ ዛሬም ያንን የወትሮውን፣ የኢትዮጵያዊነት፣ የአንድነት፣ የነፃነት አፍቃሪነት፣ በራስ-የመተማመንና የአይበገሬነት ባህሪዎቹንና፣ ተሰጥኦውን እንደገና ሊያለመልማቸው፣ በግብሩ ሊገልጣቸው፣ ህያው አድርጎ ሊጎናጸፋቸው፣ ተግባራዊ መመሪያውም ሊያደርጋቸው፣ እሱነትን፣ ከቡርነቱን ሊያረጋግጥበቸው ይገባል። ይችላልም።

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የዚህ ውጥንቅጡ የወጣ፣ በግለኞችና በስግብግቦች፣ በኃይለኞች የሚሽከረከር ዓለም መሳለቂያ፣ በሄድንበት ስፍራ ሁሉ ተንቀን የምንዋረድና የምንረገጥ፣ እንደ ርጋፎ የምንጣል፣ ሰብዓዊ ክብር የተነፈግን፣ ... ልንሆን አይገባም። ሀገራችን ዉስጥ የተፈጠሩ የጎሰኞችና አምባገነኖች መጫወቻ ሆነን እስቀጠልን ድረስ ደግሞ ስደትና ውርደት የማይቀሩልን ስለሆነ፣ ... የውጭው አደገኛ ሁኔታዎች የሚያስከትሏቸው ጉዳትና ውርደቶች ያሳድዱናል። እስቲ ለዚህ ያበቃንን ሁኔታ እንመርምር፣ እንወያይ፣ እንደማመጥ፣ ለድል የሚያበቃውን የአንድነት መንገድ፣ የመደራጀትን፣ የመሰባሰብን፣ የትብብርን፣ ... ፍቱን ጎዳናን፣ እንያዝ።

ዛሬ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በበርካታ መሠረታዊ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች እጅግ በጣም ቅስሙ ተሰብሯል፣ ተጎሳቁሏል፣ ተጎድቷል። ከጥቂት የገዥዎቻችን ግብረአበሮችና ዘራፊዎች በስተቀር አብዛኛው ሕዝብ ነጻነት አልባ፣ መብት አልባ ተደርጓል። ሃሳቡን በነፃነት መግለጥ፣ ነጻ ሆኖ መሰባሰብ፣ ሠላማዊ ሠልፍ እንኳን ማድረግ አይችልም። ገዥዎችን ደግፎ ለማጨብጨብ ካልሆነ በስተቀር!? ታፍኖ የተያዘውና እየተበደለም እየተበዘበዘም ያለው በህወሓት/ኢህ አዴግ መንግሥትና በስርዓቱ ተጠቃሚዎች ነው። ህወሓት በሚቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት፣ በነጋና በጠባ፣ የሚያኾጎደጉደውን የሃሰትና የዕብለት ዲስኩር፣ እንዲሁም በቅርቡ ከአንዲት የተደናገረች የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን የተቀባጠረውን አስቂኝ አነጋገር ቁብ ሳንሰጥ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው ራሱ በዴሞክራሲያዊ መንገድና ሕዝቡ በነፃ፣ ርትዓዊ፣ ተዓማኒነት ባለው ምርጫ በመረጠው መንግሥት አይደለም። በተጭበበረ መንገድ ራሱን በሥልጣን ኮርቻ ላይ ባንዘራፈጠ ቡድን እንጂ። ይህን የባዕዳን ተላላኪ የሆነ ገዥ ቡድን በጭፍን የሚደግፉት እነሱን ስለሚያገለግላቸው ነው። ለነገሩ በለንደኑ ሤራ አማካኝነት እንሱው ናቸው አቅፈውና ደግፈው በኢትዮጵያውያን ላይ የጫኑት። እባካችሁ ባዕዳንን አናምልክ፣ በሀገራችን ጉዳይ አዛዥና ናዛዥ አናድርጋቸው። እኛው ባለቤቶቹ እንወቅበት። እኛ ተሰባስበንና ተጠናክረን ሲያገኙን እኮ የዛሬ ሎሌዎቻቸውን እንደጋለ አሎሎ ወርውረዋቸው ነው ወደ እኛ የሚመጡት።

እንኳን ባለታሪክ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ማንም ህዝብ፣ በአምባገነኖች እጅ መዳሸቅ የለበትም። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ደጋግሞ በገድሎቹ እንዳረጋገጠው ነፃነት ወዳድ ስለሆነ በጭራሽ በአምባገነኖች መገዛት የሌለበት ሕዝብ ነው። ሆኖም ግን አብሮ መቆም በተሳነው ቁጥር ሁሉ፣ የከፋፋይ መሳፍንትና ነገሥታት ሰላባ ሆኗል። ከ 1966 እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስም ደርግ በተባለው ጨፍጫፊ ወታደራዊ አምባገነን መዳፍ ስር ሲዳሸቅ ኖሯል። ዛሬ ደግሞ ለነፃነቱ፣ ለመብቱ፣ ለሀገሩ አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ለጥቅሞቹ፣ ፍጹም ደንታ በሌላቸው ጎሰኞችና አምባገነኖች መዳፍ ሥር እየዳሸቀ ነው። ይህ ነገር በኛ በኢትዮጵያውያን የተደራጀ የአንድነት ትግል ማብቃትና ሁኔታዎችም እንደገና ላይደገሙ መለወጥ አለባቸው።

እንደዛሬዎች ጎሰኛና ለሀገር አንድነት ደንታ የሌላቸው ባይሆኑም፣ የቀድሞ ነገሥታት ገዥዎቻችንም አምባገነናዊ ነበሩ። የዛሬዎች የከፉና የባሱም እየሆኑ፣ "አንድ ወጣት ትውልድን ያጠፋው" የደርግ መሪ የነበረው፣ መንግሥቱ ሃይለማርያም እንኳን፣ ታሪክን በማያውቁ ወይንም በዘነጉ ወገኖች ስሙ በበጎ እየተነሳ ነው። የዛሬዎቹ ልክ እንደ እሱ ገዳዮችም፣ ከሱ በባሰ ደግሞ ሀገርን አጥፊዎችም፣ በመሆናቸው ነው እንዲህ ያለውም ከቅርብ ታሪክ ያለመማር የተከሰተው፣ በጣም ያሳፍራል!! መንግሥቱ በትውልድ መምተር ለፍርድ መቅረብ ያለበት ወንጀለኛ እኮ ነው!!

አሁን ወደ ዛሬው ችግር ልመለስና ያለምንም ጥርጥር በረጅም ታሪኩ ዉስጥ ማንነቱን የተቀዳጀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብስል፣ ብልህ፣ ቻይና ሃያል ነው። በዚህ ከተማመንን፣ ችግሩ ያለው በሕዝቡ አብ(ብ)ሮ አለመቆም፣ አብሮም ሁኔታዎችን በሚመጥን ብቃት አለመደራጀቱ፣ በአንድ ላይም ጥረቶቹንና ትግሉን አጣምሮና አቀነባብሮ አለመነሳቱ ላይ ነው ማለት ነው።

ይህን ልንለውጠው የምንችል ጉድለት ስለሆነ፣ በጽሞና ተነጋግረን፣ ተግባብተን፣ ልናሟላው ይገባናል እላለሁ። እንችላለንም ብዬ አምናለሁ።

ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ሃያልነትና ብልህነት አረጋግጦ፣ ነፃነቱንና ሙሉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን እንዲቀዳጅ፣ የተነጠቀውን ከዜግነቱ የሚመነጩ ጥቅሞቹን በራሱ ትግል እንዲያገኝ፣ ራሱንም የሀገሩ ባለሙሉ ሥልጣን ባለቤት ለማድረግ እንዲችል፣ ሁላችንም ተባብረን እንድንሠራ የማይሰበር ቃል እንድንገባ ሁሉንም በአክብሮት እጠይቃለሁ። ዛሬ በሀገራችን ዉስጥ ለተፈጠረው ሁኔታ ሁላችንም፣ በፈጸምናቸው የተሳሳቱ ተግባሮች፣ አለዚያም ማድረግ ሲገባን ሳናደርግ በቀረነው ግድፈታችን የተነሳ፣ ተጠያቂዎች ነን። አሁን ደግሞ የሀገራችንንና የወገናችንን የወደፊት ዕድል ለማቃናት የምንችለው እኛው ራሳችን ብቻ መሆናችንን ልንጠራጠር አይገባንም። ባለቤቶች ነን እኮ!! በቅርቡ በውገኖቻችን ላይ በደርሱት አሰቃቂ ግድያዎችና ጉዳቶች ሁላችንም በአግባቡ መቆጣታችን፣ መጮሃችንና ማልቀሳችን ተገቢ ቢሆኑም፣ ስለሆኑም መደረጋቸውን ባንቃወምም፣ ግን በፍጹም <u>በቂ</u> አይደሉም። በመናደድ፣ በመጮህ፣ በማውገዝ፣ በማዘን፣ በማልቀስ፣ በመሰለፍ፣ ሻማ ሆነ ጧፍ እያበራን በመጸለይ ብቻ ሁኔታዎችን አንለውጥም። በተጨማሪ ማድረግ የሚገቡን ነገሮች አሉ፣ በኔ እምነት እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. በሀገራችን ዉስጥ በአፋጣኝ መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ከባድና ዉስብስብ፣ ፈርጀብዙ ችግሮች መኖራቸውን ዛሬ በርከት ያለው የሕዝባችን ክፍል፣ የተደራጀውም፣ ያልተደራጀውም ክፍል፣ ስለሚያውቀው፣ የወደፊቱ ሥራችን በአመዛኙ ***<u>ለችግሮቻችን መፍትሄዎችን</u>*** መፈለግና ማግኘትም ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ችግሮቻችንን ዘርዝረን ስለመፍትሄዎቻቸው መነጋገር ያሻል።

2. በመጀመሪያ መኖራቸውን ለምንተማመንባቸው የጋራ ችግሮቻችን መፍሄዎችን ለማግኘት መጣር ያለብን በውይይትና ***<u>በሠላማዊ መንገድ ቢሆን ይመረጣል፣</u>*** ይሻላል ብዬ ስለማምን፣ የሠላሙን ጥረት ሁሉ ለመሞከር ልቦናችንና በራችን ክፍት ሊሆኑ ይገባል። ጠብን መጀመር፣ ጥላቻን ማራገብ፣ በአግላይ መንገዶች መጓዝ፣ መራራቅን መፍጠሩና መቃቅርንም ማጠናከሩ ስለማይቀር፣ ለሁላችንም አይጠቅመንም፣ ግድ ሲሆንብን ደግሞ፣ የጠብ መንገዶቹ አይጠፉንም።

3. ሁሉም በጎሊናው የሚገዛ፣ በግለኛነትና በመስገገብ፣ በጥቅም፣ በዘር ፖለቲካ፣ ያልተቀየደና ያልታወረ ኢትዮጵያዊ (ዜጋ) ችግሮቻችንን በጋራ በምንፈታበት መንገድና፣ እንዲሁም በይበልጥ በመሰባሰብና በአንድነት በመንቀሳቀስ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት ላይ ሃሳብ የሚለዋወጥበት ***<u>መድረክ</u>*** በፍጥነት ሊፈጠር ይገባል። ሁሉም የሚታወቁ ድርጅቶች፣ ኅብረቶችና ጥምረቶች፣ በተናጠል እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የዕምነት ተቋማት፣ ጉልህና ጠቃሚ ሀገራዊ ሚና እየተጫወቱ ያሉ ግለሰቦች፣ ሊጋበዙ ይገባል።

4. መድረኩ ማንንም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅት፣ ወይንም በሀገራዊ ጉዳዮች ገንቢ ሚና እየተጫወተ ያለ ዜጋ፣ ***<u>በቅዲሚያ የሚያገል</u>*** ሊሆን አይገባም። የምንሰባሰበው ***<u>በኢትይጵያዊነታችን፣ ስለጋራ ሀገራችንና ወገናችን</u>*** ችግሮችና ችግሮቹም ሊፈቱ ስለሚችሉባቸው መንገዶች ለመነጋገር ስለሆነ፣ በሠላማዊና ፖለቲካዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁ የሆኑ የህወሓት/ኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም ከተገኙ ከመድረኩ ሊገለሉ አይገባም። እነሱም ኢትዮጵያውያን ናቸው ብለን ስለምናምን፣ ቅን ልቦናና

ድፍረቱን አግኝተው ወደ መድረኩ እንዲመጡ ለማድረግ ከተቻል፣ እሰየው ነው። የምንቃወመው የጥፋት ተግባሮቻቸውን ነውና!!

5. በሚዘጋጀው የጋራ መወያያ መድረክ ላይ ማንኛውም የተደራጀ ኢትዮጵያዊ ሃይል፣ በሲቪክ ማህበር ይደራጅ ወይንም በፖለቲካ ድርጅት፣ የድርጅቶች ኅብረት ወይንም ጥምረት ሆኖ እየሠራ ያለ፣ ኅብረ-ብሔር ድርጅት ይሁን በብሄር መልክ ይደራጅ፣ እንዲሁም መስፈርቶችን የሚያሟላ ግለሰብ ... ይሻላል ስለሚለው የትግል ስልትም ሆነ ስለሌሎች ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ጉዳዮች ማናቸውንም ሃሳብ ለማቅረብ መቻል አለበት።ህወሓት ሕጋዊ የሚል ስሞ ሰጥቶ ተነጥለው እንዲቆሙ ያደረጋቸው ድርጅቶችም ራሱ ህወሓት የማያከብራቸው አሳሪ ህግና ደቦችን ገድብ ለመጣስ ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል። አሁን ያሉበት ሁኔታ እውን ለውጥ ሊያመጡበት የሚያስችል ነው? **<u>በሚመርጠውም ሆነ በሚከተለው የትግል ሥልት ወይንም በተደራጀበት ቅርጽ የተነሳ፣ ወይንም በሕዝቡ ዓይን ሕጋዊነቱን እያጣ ያለው ህወሓት በሚለጥፉቸው ስያሜዎች የተነሳ</u>** ከመድረኩ ሊገለል አይገባም። ኢትዮጵያዊነት የተገነባውና የሚለመልመውም በልበሰፊነት፣ በሁሉንም አቃፊነት፣ አካታችነት፣ አሳታፊነት ላይ ነው።

6. መጀመሪያ መንደርደሪያ ሃሳቦችን በዘመናዊ መገናኛ መንገዶች በመለዋወጥ፣ ግንኙነትን መጀመር ይቻላል። ከዚያ በስምምነት መድረኮችን ማጠናከርና አንድ **<u>ትልቅ ስብሰባ</u>** (መለስተኛ ጉባዔ) የሚደረግበት ሁኔታን በጋራ ማመቻቸተት ያስፈልግ ይሆናል። ተቃውሞ ከሌለ፣ ቀዳሚነቱን ወስዶ፣ የመጀመሪያውን ስብሰባ ኢሕ አፓ ዴሞክራሲያዊ በአባልነት የሚሳተፍበት፣"የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ" ( ሸንጎው)፣ ሊጠራው ቢችል ጥሩ ነው ብዬ አምናለሁ። ቁምነገሩ በሀገራችን ችግሮችና በመፍትሄዎቻቸው ላይ ተሰባስቦ ለመምከር መቻሉ ላይ ነው። ማንም ይጥራው ማን በቅንነት ለመሰባሰብና ለመወያየት እንቻል፣ መፍሄዎች አይታጡም። እንደ እውነቱ ከሆነ እስከዛሬ ተጃጅለን ቆይተን ይሆናል እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን በዕውቀት፣ በብልኅነት፣ በተመክሮ ... ከሌሎች ሀገሮች ብንሻል እንጂ፣ አናንስም። ሃሳቤን ያቀረብሁት በቅንነትና በትህትናም ነው። ገንቢ በሆነ መንገድ የሃሳብ ልውውጥ እንደምናደርግ ተስፋ አለኝ። ያለውን ከወረወረ ሰው ፈሪ አይባልም ስለሚባል፣ እኔም ጭንቀቴን ከእናንተ ከወገኖቼ ጋር ለመካፈልና ወደ መፍትሄ ፍለጋም ለሚደረገው ጉዞ ትንሽ ከጠቀመ በሚል ሃሳቤን በግርድፉም ቢሆን ሰንዝሬአለሁ።

መርሻ ዮሴፍ
ms38498@yahoo.com